# የጎንደር ህብረት ሊቀመንበር ንግግርና  እንድምታቸው።

አስቴር ጫቅሌ( አትላንታ )

" ጅብ ከማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" "  ሰው የለም ወይ በሀገሩ"" የቄስ ሚስት አውቅሽ አወቅሽ ቢሏት መፃህፍን አጠበች" " ትንሽ ጭንቅላት አደገኛና መርዝማም  ነው" " ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር"

የጎንደር ህብረት ሊቀ መንበር አቶ አበበ ንጋቱ በሜነሶታ ያደረጉትን የወረደ ለህገራችን ፖለቲካ የማይመጥን አሳፋሪ የሆነውን ንግግራቸውን ስሰማ የተሰማኝ ከላይ የፃፍኩትን የሀገራችን ብሂሎችና አባባሎቹን ነው ያስታወሰኝ። ያዘንኩት ጎንደር ስንት የተማሩ ለሀገራቸው የሚሰሩና የሚተጉ ሰዎች እንደለሉበት እንዲህ አይነት ሰውና መሰሎቹ የፖለቲካውን  ቦታውንና ምህዳሩን አራጠው ይዘው የሀገራችንን ፖለቲካ እንዴት ደረጃውን ዝቅ አድርገው እንደሚቦክትና እንደሚጨማልቁት  ስመለከት አዝናለሁ። ሰው የለውም ወይ በአገሩ ያሰኛል።

የአቶ አበበ  ንጋቱ ተራ ንግግር ምንጭ ምነድነው? የዕውቀት ፣ የግንዛቤና የአመለካከት ችግር ነው ወይስ  የተለየ ጉዳይ ነው የሚለውን እንመልከት። ከንግግራቸው በሰፊው የተሰመረበትና ብዙ ህዝብ ያነጋገረው " አንዳንድ ወገኖች አማራው በአማራ ማህበር አንድ ሁኖ መደራጀት ሲገባው ለምንድን ነው ጎንደር፣ጎጃም፣ሸዋና ወሎ ህብረት እያላችሁ የምትከፋፍሉን" ይሉና ለዚህ እርሳቸው የሚፈልጉትና የሚራምዱት አደረጃጀት አስፈላጊነቱንና ጠቃሚነቱን ከማስረዳት ይልቅ አማራ አማራ እያሉ የሚጮህት ከጀርባችው ያለ ህዋት ወያኔ ሰለመሆኑና የደጉ አንዳርጋቸው ልጆች ናቸው በማለት  የጎንደርን ሕዝብ የማይመጥን ክስና ስድብ ያቀርባሉ።  አቶ አበበ በመቀጠል ሀገራችንን ለነፃነትና ለድል ማብቃት የምንችለው በዘር በመደራጀት ሳይሆን በክፍለ ሀገር በማደራጀት ማለትም የጎንደር፣የጎጃም!የወሎ፣የሸዋ፣የአሩሲና፣የሐረር፣የወለጋ፣ወዘተ ህብረት በመዳራጀት ነው እንጅ በዘረኝነት የሚደረገው አደረጃጀት አደገኛና ወያኔዊነት ሲሉ አዲሱን የትግል ማኔፌስቷቸውን ነግረውናል። በመቀጠል የአማራ ማንነትና ብሶት ያነሳሳቸውን ወጣቶችን የወያኔ ሰላይና ደህንነቶችን ሲሉ በተደጋጋሚ ይከሳሉ። የሚስገርመው አማራውንና ኢትዮጵያዊነትን ለመስደብና ለመክሰስ ሲሉ  የኦሮሞ አክትቢስት የሚባሉትን አቶ መሀመድን ከዳላስ ቴክሳስ ጭነው በመውሰድ በጎንደር ህብረት ወጭ ለሜኖስታው ስብሰባ የክብር እንግዳ ተናጋሪ አድርገዋል። አቶ አበበ ከኦነግ  ህዝብ ጋር ያላቸውን አጋርነት ለማሳየት በአማራው ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ስድብና ተቃውሞ ሲነሱ

ስለ ኦነግ ፅንፈኝነት፣ ሀገር የመገንጠልና የመበተን አደጋ ግን አንድም ቃል አልተነፈሱም ። አቶ አበበ ንጋቱ ይህ የተዘበራረቀና ለአለንበት ትግል የማይመጥን ብስለት፣እውቀትና አስተዋይነት የጎደለው ንግግራቸው ምንጭ ምንድን ነው? የጎንደር ህብረትስ ለዚህ አላስፈላጊ ለሆነውና ከራሱ ህዝብ ጋር ለሚጋጨው ንግግር ምን ይጠበቅበታል የሚለውን እንይ።

አንደኛ/ አቶ አበበ ንጋቱ በሜኖሶታው ስብሰባ ስለ አማራው ተጋድሎና ድርጅት ያቀረቡት ክስና ስድብ የጎንደር ህብረት እንደ ድርጅት መንፈሱን ይጋራዋል ብየ አላምንም። ምክንያቱም ለጎንደር ህብረት ከአማራው ድርጅት በላይ ሌላ አካልና አጋር ይኖረዋል ብየ አላምንም። የጎንደር ህብረት በአደረጃጀቱ፣ በዓላማና በመርህ ደረጃ ትልቅ ችግር አለበት ይህን ወደ ሆላ እመጣበታለሁ።አቶ አበበ ንጋቱ ግን በሜኖሶታው ንግግራቸው ያንፀባረቁት የጎንደር ህብረት ሊቀ መንበርነታቸውን በመጠቀም ሌላውን ጃኬታቸውን የግንቦት ሰባት በአባልነታቸውና በደጋፊነታቸው በውስጣቸው የደበቁትን ጃኬታቸውን በማውጣት ነበር በአማራ ድርጅቶች ላይ የስድብ፣የጥላቻና የብቀላ ቅላፄ ባለው ባልተሞረደና ባልተገረዘ አደበታቸው በአማራ ድርጅትና ወጣቶች ላይ ያነጣጠረ ንግግር ያደረጉት። እንደ ሚታወቀው ግንቦት ሰባት የአርበኞች ንቅናቂ የሚባለው በጎንደር በወልቃይት፣ማይ ፀብሪ፣ሁመራ ላይና ታች አርማጭሆ ህዝቡ ለማንነቱና ለነፃነቱ የሚደርገውን ትግል ግንቦት ሰባት የእኔ ንቅናቂ ሲል የአማራ ወጣቶች የዚህ ተጋድሎ አካሎች የሆኑት ግንቦት ሰባት በሀሰት የሚቀርበውን ሪፖርትና መግለጫ ሲቃወሙና ሲጣጥሉት ነበር። አሁን ግንቦት ሰባት በጎንደር በሚካሄደው ትግል ቢቻል መሪው እርሱ ነው ለማለት ካልተቻለ አለበት ለማለት በጎንደር የሀሰት ሪፖርት የሚቀርብላቸው ሰው እንዲመለምሉና የወልቃይትን የማንነትና የአማራውን ተጋድሎን ለዚህም የሚሞቱና ደማቸውን የሚፈሱ ጀግኖችን ለግንቦት ሰባት ድርጅት አሳልፎ በመሸጥ ድርጅቱ ማለት ግንቦት ሰባት በውጭ ሀገር በዲያስፖራ በሚደርገው የገንዘብ ዝርፊያ ሽርክና በመግባት የጎንደር ህብረትን መጠቀሚያ ለማድረግ ነው። አቶ አበበ ንጋቱ እንደ መከራከሪያ አድርገው የሚቀርቡት ጎንደር የአምስት የተለያዩ ነገዶችና ብሔሮች አገር ስለሆነ አማራ ብሎ በመደረጃት ሌሎች ነገዶችን ማግለል ነው ይሉናል።አሉ የሚሉአቸው ነገዶች ቅማንት ይሉና ሌላውን ነገድ ሶስት ግዜ ደራርበው አንድን ነገድ ሶስት ጊዜ ይጠሩታል ማለት ጉምዝ ፣ሻንቅላና ወይጦ በማለት ለማወናበድ ይሞክራሉ። የአማራ ሊህልቃን አማራ በማለት በአማራ ስነ ልቦናና ባህል የኖረና ከዘመናት ጀምሮ በዚህ መንፈስ የሚኖር ማለት ነው። ይህም ሁኖ እነዚህ ጥቃቅን

ነገዶች ከጠቅላላው የጎንደር ህዝብ እጅ ሲነፃፀር ሁለት ፐርስነት አይሞላም ስለዚህ የጎንደር ህዝብ በአማራነቱ በመደራጀት እየተካሄደበት ካለው የዘርና የትውልድ ጥፋት ለመከላከል ፣ በሚካሄደው የፍትህና የነፃነት ትግል ባለድርሻ መሆን ፍትሀዊ መብቱ ነው። ችግሩ የአቶ አበበ ንጋቱ ድርጅት ግንቦት ሰባት የአማራው ማህረተሰብ በማግለል በእዳጣን ብሄረሰቦች ስብስብ ሁኖ ትልቁን ህዝብ አማራውን ከፊት ሁኙ እየሸፈርኩ አማራውን ገንዘቡንና ደሙን እየተጠቀምኩ ልኖር በሚለው አካሄድ አቶ አበበ ንጋቱ እራሳቸውን በቅማትነታቸው እንደ ተጨቆኝ በመቁጠር ማለት በአማራው ህዝብ ቂምና ጥላቻ በመቆጠር ግንቦት ሰባት በአመራርነትና በአካልነት ካሰባሰባቸው ተጨቆኝ ጎሰኛ ነን ከሚሉ በአንድነትና በኢትዮጵያ ባንዴሬ የተሸሸጉት አጋር መሆናቸውና ከዚያ አልፈው በጎንደር ህብረት ስም አማራው በማንነቱ እንዳይደራጅ ተልእኮ ይዘው ፀረ አማራ ንቅናቂ ማድረጋቸው ነው። ቢያንስ አቶ አበበ ንጋቱ ፅንፈኛና ዘረኛ ተብሎ ከሚከሰሰው ከአቶ ጅዋር መሀመድ ለአማራው ህዝብ የተሻለ ቅን ልቦናና አመለካከት ሊኖራቸው ይገባ ነበር ።ጅዋር መሐመድ በቅርቡ ባደረገው ቃለ መጠየቅ አማራው በማንነቱ ተደራጅቶ የሚካሄደው ትግል ፍትሀዊ በጣም ተፈላጊ ነው። ለዚህ የማንነት ጥያቄና አደረጃጀት ዋጋ ተከፍሎብታል ነገር ግን ይህን በአማራ ብሄርተኝነት የተፈጠረውን አደረጃጀት ዝቅ በማድረግ በክፍለ ሀገርና በጎጥ ኣንዲደራጅ ማድረግ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ይለዋል።

ሁለተኛ/ ሌላው ችግር የጎንደር ህብረት የአደረጃጀት መርህ ( principle ) ነው። ይህ ህብረት እንዴት ተቋቋመ ? ለምን ዓላማ? አሁን እያደረገ ያለው ተግባርና አደረጃጀት ከህብረቱ ዓላማ ጋር ይሄዳል ወይስ ይቃረናል?ከማህበሩ በስተጀርባ ምን አለ የሚሉትን ማየት ጠቃሚ ነው። ህዋት ወያኔ ህዝብን ከፋፍሎና አዳምቶ ለመግዛት ካለው እቅድ የተነሳ የቅማንትን ማህብረተሰብ ውስጥ ለውስጥ በማደራጀት የማንነትና የግዛት ክልል በማንሳት ከአማራው ክልል መሰተዳድር ጋር ወደ ግጭት ማምራቱ ይታወቃል ። በዚህ ጊዜ በውጭ ዲያስፖራ የአሁኑ የጎንደር ህብረት ሊቀመንበርን ጨምሮ በእሳት ራዲዮና ቴሌብጅን ይህ ንቅናቂ የቅማንት ህዝብ የማንነት፣ የመብትና የነፃነት ታጋዮች በአማራው ክልል በመተማ በአርማጭሆና በጭልጋ ይህን ያህል ወታደሮች ገደሉ ማረኩ እየተባለ ስለ ጀግንነታቸውና ተጋድሎቸው የዜና ዘገባ ይቀርብልን ነበር። እንደገና ነገሩ ተገለበጠና በህዋት ወያኔ የተደራጅ ጽሕፈት ቤታቸው ትግራይ የሆነ በህዋት ወያኔ የሰለጠኑ የቅማንት መብት አስከባሪ ነን በሚሉ ዜናው ተተካ ።ያም ሆነ ይህ ችግሩ ሰፍቶና ተለጥጦ በአማራው ህዝብና በቅማንቱ ወደ እርስ በእር ግጭት ሲመራ

የአካባቢው በተለይ ሙሉ በሙሉ የቅማንት ተወላጅ የሆኑት ይህ ግጭት በጣም ከመስፋቱ ና ብዙ የወገኖቻችን ደም በሁሉም አቅጣጫ ከመጥፋቱ የተነሳ እርቅና ሰላም ማምጣት አለብን በማለት የጎንደር ህብረት ፈጠሩ። ችግሩ ለመፍታት የሚባለውንና እየተነገረ ያለውን ያህል ባይሆንም በተወሰነ ደረጃ አስተዋፅኦ ሁኖአል።ችግሩ ግን ሙሉ በሙሉ አሁንም አልተፈታም። የጎንደር ህብረት የቅማንት ተወላጆች በዘመዶቻቸው ላይ ምክርና ተገስፅ በማድረግ የተጎድትን ቤተሰቦች በትንሹ በመርዳት መልካም ግን እንደሚጋነነው ያልሆነ ስራ በመስራታቸው ሊመሰገኑ ይገባል። ከላይ እንደገለፅነው የጎንደር ህብረት ሁለት የስቢክና የሰብዓዊነት ስራ ብቻ ነበር የሰራው ይህም የማህበሩ መርህና አላማ ስለሆነ ነው። የተሰሩት ስራዎች አንደኛ እርቅና ሰላም ማምጣት፣ ሁለተኛ በግጭቱ የተጎዱ ወገኖችን መርዳትና መልሶ ማቋቋም ነው። ይህ ቀጣይነት ያለው ስራ ነው። ማህበሩም ጎንደር ህብረት ከዚህ የተለየ ውክልናና ድርሻ አይኖረክም። ስራውም የተቀደሰና ሰፊ ተከታታይነተ ያለው ነው። ይህን ማህበር ጎንደር ህብረት ወደ ተለየ ግን የማይወጣውና የማያዋጣው ችግር እያስገቡት ያለው አሁንም የህብረቱ ሊቀመንበር አቶ አበበ ንጋቱ ና በእርሳቸው የሚመራው የህብረቱ ካብኔ ነው ። በወልቃይት የማንነት ጥያቄና ኮረኔል ደመቀ ዘውዱ ያበሰረወን አብሪ ጥይት በዚያው የተቀጣጠለው የአማራ የማንነት አመፅ፣ በጎንደርና በባህር ዳር የተደረገውን መሪት እንቅጥቅጥ የተቃውሞ አመፅ በውጭ ሀገር በጎንደር ህብረት እጅ ወደቀ። የጎንደር ህብረትም ብዙዎች የህብረቱ አመራሮችና ተወላጅ ባላወቀው ሁኔታ ግንቦት ሰባት እጅን አስገባ። የቅማንትና በአማራ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ብሎ የተቋቋመው ጎንደር ህብረት ሜዳው ባዶ ሁኖ ሲገኘው የዚሁ የወልቃይት የማንነት ጥያቄና የአማራው የአመፅ ንቅናቂ ተወካይ እኔ ነኝ በማለት የግንቦት ሰባት አባላትን በየስቲቱ የቻብተር አባል በማድረግ ስሜቱ የተነሳሳውን በእነ ኮረኔል ደመቀ ጀብድ የተነቃቃውን ህዝብ ቀስቃሽና አነሳሽ የሆነውን የእነ ፋሲል ደመወዝ፣መሀሪ ደገፋው፣ሻንበል በላይንና ይሁኔ በላይ ዘፈን በመጠቀም በቀጥታ ገንዘብ ማሰባሰብ ተጀመረ ቢያንስ እሰከ ሰባት መቶ ሺህ ብር ተሰባሰበ። ጎንደር ህብረት የነበረውን ክፍተት በመሙላት ያደረገውን የገንዘብ ማስባሰብ ሊስመሰግነውም ሊስወቅሰውም የሚችለው የት፣መቼና ለነማን እንዳዋለው ሲታይና ሲታወቅ ነው። ሆኖም አሁን ያለው የጎንደር ህብረት የጎንደርን ግዛት የሚወክል አይደለም። ቀደም ሲል እንደ ተገለጠው በቅማንት ህዝብና በበአማራው ህዝብ የነበረውን ግጭት ለመፍታት በአካባቢው ተወላጆች የተቋቋመ የሲቢክ ድርጅት ነው። ይህ የሲቢክ ድርጅት ወደ ሌላ አይነት ድርጅት ተለውጦ ከሆነ

በግልፅ መታወቅ አለበት። ጎንደር ሲባል በጣም ሰፊ ነው። ሰባት ትልልቅ አውራጃዎች ከአስር ሚሊዮን ህዝብ ያለው ነው። ስለዚህ በመርህ ደረጃ አሁን ያለው የጎንደር ህብረት ከአንድ አካባቢ የመጡ ለተወሰነ አላማና ግብ ብቻ የተሰባሰቡ ወንድሞች ጎንደርን አይወክሉም ። ቅን አመለካከትና ልቦና ካለ በየስቲቱ በየ ቻበተሩ ሁሉን ጎንደሪ የሚጠቀልል መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ ና ስራ ተሰርቶ ነው የሁሉንም ጎንደሪ ውክልናና ተሳትፎ ማግኘት የሚቻለው። አሁን ያለው የጎንደር ህብረት በአንዳንድ ስቴቶች የተሰራው ጥቂት የመንደር ሰዎች የግንቦት ሰባትን አባላት በማማከል ነው ቻብተርና ምክር ቤት ያቆቆሙት። አንድ ስቴት ላይ ያየሁት ቻብተር አመራሩ አምስት ናቸው።ሶስቱ ከግንቦት ሰባት የመጡ ሁነው ሁለቱ ፋሲል ግንብና የጎንደረን ዋርካ የሚውቁት በፎቶ ነው ። ለምንድን ነው ብየ የቻብተሩን ሊቀ መንበር ስጠይቅ ቅድመ አያታቸው የሁለቱም ከጎንደር ነው አለኝ። እንዴት  የህዝቡን ስነ ልቦና ካላወቁ የገበሬውን ህይወተና  ባህል አፈሩን ውሀውን ካላወቁ እንዴት ነው መሪ ይሆናሉ ብየ ስጠይቅ መልስ የለውም በወሩ የጎንደር ህብረት የፈንድረይዝግ ዝግጅት ተደረገ አትላንታ የቀረ የለም ከበራፍ እስከ ገንዘብ ማሰባሰቡ እስከ  መደረክ ቅንብሩ ትብብሩ አስደሰተኝ ግን ፈራሁ ገንዘብ ና ግንቦት ሰባት ፍቅራቸውን ስለማውቅ ይህን ሀሳብ ያጠናከረልኝ የህብረቱ ሊቀ መንበር አቶ አበበ ንጋቱ ከአዲስ ድምፅ ጋር  ባደረጉት ቃለ ምልልስ ደግመው ደጋግመው የነገሩን በደም ፍላት የአማራ ድረጅቶች እሳት ሜዲያንና ድርጅቶችን ይሳደባሉ ይላሉ ።ድርጅት ሲሉ ግንቦት ሰባት ማለታቸው ነው። ማጠቃላያ የጎንደር ህብረት በአስቸኳይ ሁሉን ጎንደሬ ያካተተ የየክልል( ቻብተር ) ስብሰባ በሰፊው በመካሄድ እነደ ገና መደራጀት አለበት።አሁን ያለው የጎንደር ህብረት ሁሉንም ጎንደሪ ያካተተ አይደለም። ለዚህ ደግሞ አሁን ባለው የጎንደር ህብረት የድርጅት ተሸካሚ ከሆኑት በቀር ለህገራቸው ቅን ልቦና ያላቸው፣ የተማሩ፣ያለ መታከት ለህገራችን የዲሞክራሲና የነፃነት ትግል  መላ ሕይወታቸውን ለትግል የሰጡ ወንድሞች በህብረቱ አሉ ብየ ስለማምን ይህን የማስተካከል እርምጃ ይወስዳሉ ብየ አምናለሁ። ሁለተኛ የጎንደር ህብረት የቅርብ አጋሩ የሚሆነው  የአማራ ድርጅት ነው። ስለዚህ ሊቀመንበር አበበ ንጋቱ በአማራው ድርጅት ያላቸው ጥላሸትና የፈጠራ ክስ የጎንደር ህብረት አቋም አለመሆኑ ማብራሪይ እንዲሰጥ ። በጎንደር ህብረት ስም የሚደረገው አላስፈላጊ ግጭት እንዲቆም በትህትናእንጠይቃለን።